# ነገረ-ማርያም

አልዓዛር
ሚራክ ገብረክርስቶስ

## ኪዳን ምሕረት
## የቃል ኪዳን ሁሉ ፍፃሜ

ባለፈው እትም እግዚአብሔር ከአሕዛብ መካከል አብርሃምን እንደመረጠ፤ አብርሃምም ከወገኖቹ ተለይቶ እግዚአብሔር ወደመራው ሥፍራ እንደሄደ፤ በዚያም እግዚአብሔር አብርሃምን ከፍ ከፍ እንዳደረገውና ለእርሱና ለዘሩ ቃል ኪዳን እንደገባለት ለመግለጽ ተሞክሯል። በዚህ ጽሑፍ ደግሞ ለአብርሃም የተሰጠውን ቃል ኪዳን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለውን ሥፍራና ተፈፃሚነት በአጭሩ እንመለከታለን።

የአብርሃምን ታሪክ በሚገልጸው በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሔር ለወዳጁ ለአብርሃም በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ ቃል ኪዳን እንደገባለት ለማወቅ ይቻላል። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለትን ቃል ኪዳን ስናጤነው በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም የገባለትን ቃል ኪዳን ስናጤነው በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም በውስጡ አራት ዋና ዋና ተስፋዎችን ይዞ ይገኛል። እነርሱም፤

ሀ. እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር እንደሚያበዛው፤

ለ. እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘር የከነዓንን ምድር እንደሚያወርስ

ሐ. እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ አምላክ እንደሚሆን፤

መ. እግዚአብሔር በአብርሃምና በዘሩ የምድር አሕዛብን እንደሚባርክ

የሚገልጹ ተስፋዎች ናቸው። እነዚህ ተስፋዎች ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ለዘሩም የተሰጡ በመሆናቸው በኪዳን አብርሃም ውስጥ ሳይጠቀሱ አይታለፉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዘር፣ የሚለው ቃል የተለያየ ትርጉምና አገባብ ቢኖረውም በኪዳን አብርሃም ውስጥ የሚኖረው ትርጉም ከሰው የሚወለድ ልጅና ትውልዱን የሚያመለክት ነው። (ዘፍ.፫+፲፭፤ ዘፍ.፳፩+፲፪-፲፫) በዚህ መሠረት የአብርሃም ዘር ሲል የአብርሃም ልጅ፣ የአብርሃም ትውልድ ማለት ነው ቀጥለን ከላይ የተጠቀሱትን ተስፋዎች በጥሩ እንመለከታለን።

ሀ. «ዘርህን...አበዛዋለሁ» እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል ሊሠራው ያቀደውን የሰውን ዘር የማዳን ሥራ ለመፈፀም የአብርሃምን ዘር ለማብዛት አሰበ። አብርሃምና ሚስቱ ሣራ በእድሜአቸው የሸመገሉ ከመሆናቸውም በላይ ሣራም መሐን ነበረች። ሁሉን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔርም ለአብርሃም ዘሩን እንደሰማይ ከዋክብት እንደባሕር አሸዋ እንደሚያበዛው፤ ሚስቱም ሣራ እንደም ትወልድ ተስፋ በሰጠው ጊዜ እንደሚፈጸምለት አመን ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት። (ዘፍ.፲፫+፲፮፤ ዘፍ.፲፭+፬-፮፤ ዘፍ.፳፪+፲፯፤ ዕብ.፲፩+፲፩-፲፪) አብርሃም ምንም እንኳን ከአጋር እስማኤልን ከኬጡራ ስድስት ልጆችን ቢወልድም እግዚአብሔር ተስፋውን የሰጠው ከሕጋዊት ሚስቱ ከሣራ በሚወለደው ልጅ በኩል ስለሆን ሁል ጊዜ ቃል ሲገባለት በዘሮችህ ሳይል «በዘርህ» ወይም ‹ለዘርህ› እያለ ስለአንድ ዘር ይናገር ነበር። ይህም የአብርሃም ዘር የተባለው በደጅ ጥናት፣ በተአምራት፣ በብሥራት እግዚአብሔር ከሣራ የተወለደው ይስሐቅና የይስሐቅ ትውልድ ነው። ይስሐቅም ተወልዶ ካደገ በኋላ እግዚአብሔር ለይስሐቅ የአባቱን ቃል ኪዳን አጽንቶለታል። (ዘፍ.፳፮+፬) ይስሐቅ ከርብቃ ሁለት መንትያ ልጆች ኤሳውንና ያዕቆብን ቢወልድም ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ለያዕቆብ ጸንቶለታል። (ዘፍ.፳፰+፬) ያዕቆብም የአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል አባት ለመሆን በቃ እንግዲህ እንደሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ የበዛው ሕዝበ እሥራኤል የተገኘው መሐን ከነበረችው ከሣራና የሞተን ሰው ከመሰለው ከአረጋዊው ከአብርሃም ነው። (ዕብ.፲፩+፲፪)

አብርሃም በሥጋ የእስራኤላውያን አባት ቢሆንም በሃይማኖት ደግሞ የአሕዛብም አባት ነው። በሥጋ የአብርሃም ልጆች የሆኑት «እሥራኤል ዘሥጋ» ይባላሉ። በሃይማኖት ደግሞ የአብርሃም ልጆች የሆኑት እሥራኤል ዘነፍስ ይባላሉ። እግዚአብሔር ለአብርሃም ስሙን በለወጠለት ጊዜ «ከዛሬ ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ። ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል። ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና...» በማለት የአሕዛብ አባት እንዳደረገው እንረዳለን። (ዘፍ.፲፯+፭) አሕዛብ ጻድቁ አብርሃም ያመለከውን እግዚአብሔርን ካመለኩ፤ የአብርሃምን እምነት ከተከተሉ፤ አብርሃም የሠራውን ሥራ ከሠሩ የአብርሃም ልጆች የተስፋውም ወራሾች ይሆናሉ። እሥራኤላውያን ደግሞ የአብርሃምን አምላክ ከደው ለጣኦት ከሰገዱ ሃይማኖታቸውን ከለወጡ የተስፋው ወራሾች መሆናቸው ይቀራል።

በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መላው የሰው ዘር ሕዝብና አሕዛብ ሳይባል በእምነት እንዲድን

www.ethiopianorthodox.org

ስለፈቀደ በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነው ተጠምቀው ከኃጢአታቸው የተቀደሱትን ሁሉ የአብርሃም ዘር የተስፋውም ወራሽ እንዲሆኑ ፈቅዶአል። ስለዚህ ለፍጹም ደህንነት የሚያበቃው ከአብርሃም በሥጋ መወለድ (እሥራኤል ዘሥጋ መሆን) ሳይሆን በዓለም መድኃኒት በኢየሱስ ክርስቶስ አምና በዳግም ልደት ከሥላሴ ተወልዶ ክርስቲያን (እሥራኤል ዘነፍስ) መሆን ነው። ይህንንም በሚከተሉት ጥቅሶች እንመለከታለን።

፭. መጥምቁ ዮሐንስ በሥጋ የአብርሃም ልጆች ለሆኑ ለፈሪሳውያንና ለሰዱቃውያን ሲያስተምር «...በልባችሁም አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ። እላችኋለሁና ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሳለት እግዚአብሔር ይችላል።» (ማቴ.፫፥፱) በማለት እንጨት ጠርበው ድንጋይ አለዘበው የሚያመልኩትንና አይምሮአቸው እንደ አለት ቀዝቃዛና ጠንካራ የሆኑትን አሕዛብን የአብርሃም ልጆች እንደሚሆኑ ገልጿል።

፮. መድኃኒታችን በሚያስተምርበት ጊዜ የአብርሃም ልጆች በመሆናቸው ኮርተው «አባታችንስ አብርሃም ነው» ብለው መልስ ለሰጡት አይሁድ ሲመልስላቸው «የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። አብርሃም እንዲህ አላደረገም... አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ አየም ደስም አለው።» ብሎአቸዋል። (ዮሐ.፰፥፴፱–፵፮፤ ፶፮) መድኃኒታችን ይህን የተናገረው በሥጋ የአብርሃም ልጆች መሆናቸውን አጥቶት አይደለም። (ዮሐ.፰፥፴፫–፴፰) አባታቸው አብርሃም ሊያየው የተመኘውን፤ እነሱ በዓይናቸው ያዩትንና በኋላም የገደሉትን ኢየሱስ ክርስቶስን አሕዛብ ሳያዩ በሐዋርያት ስብከት አመኑበት።

ስለዚህ በሃይማኖት የአብርሃም ልጆች የተስፋውም ወራሾች ለመሆን በቁ።

፯. ቅዱስ ጳውሎስም አሕዛብ በእምነት የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ ሲገልጽ «እንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ እወቁ። መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። እንግዲህ ከእምነት



የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ። ብሏል። (ገላ.፫፥፮–፱፤ ፳፫፥፳፱፤ ሮሜ.፬፥፩–፳፤ ፲፩–፳፭) ዳግመኛም በሮሜ.፱፥፮–፰ ላይ «እነዚህ ከእሥራኤል የሚወለዱ ሁሉ እሥራኤል አይደሉምና የአብርሃም ዘር ስለሆኑ ሁሳቸው ልጆች አይደሉምና። ነገር ግን በይስሐቅ ዘር ይጠራልሀል ተባለ። ይህም የተስፋ ቃል ልጆች «ዘር» ሆነው ይቆጠራሉ እንጂ እነዚህ የሥጋ ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም ማለት ነው።» በማለት የአብርሃም ዘር የእግዚአብሔር ልጆች መሆን የሚቻለው በሃይማኖት እንጂ በሥጋ ከአብርሃም መወለድ ብቻውን ለበረከትና ለዘለዓለም ሕይወት እንደማያበቃ አረጋግጦአል። ስለዚህ አብርሃም በተሰጠው ተስፋ መሠረት የሕዝብና የአሕዛብ አባት በመሆኑ ዘሩ እንደሰማይ ከዋክብት እንደምድር አሸዋ በዝቶለታል።

፰. «ይህችን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ» እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሩን እንደሰማይ ከዋክብት እንደባሕር አሸዋ እንደሚያበዛለት ቃል ኪዳን ሲሰጠው ዘሩ (ትውልዱ) የሚኖርበትን ቦታም አዘጋጅቶለታል። በዚህ መሠረት በየቃል ኪዳኑ ለአብርሃምና ለዘሩ ርስት አድርጐ የከነዓንን ምድር እንደሚሰጠው ነግሮታል። «ዓይንህን አንሣና አንተ ካለህበት ሥፍራ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ወደምሥራቅና ወደ ምዕራብ እይ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁ» ብሎታል። (ዘፍ.፲፫፥፲፬–፲፰፤ ዘፍ.፲፯፥፯፤ ዘፍ.፲፰፥፲፰–፳፩) አብርሃም ይህን ተስፋ ያገኘው በከነዓን እንደመጻተኛ በሚኖርበት ሰዓት የእግሩ መረገጫ የምታህል ርስት በሌለው ጊዜ ሲሆን አብርሃም እግዚአብሔር የነገረው ሁሉ እንደሚፈጸምለት በማመኑ ጽድቅ ሆና ተቈጠረለት። እግዚአብሔር ይህንኑ ተስፋ ለይስሐቅና ለያዕቆብም አጽንቶላቸዋል። (ዘፍ.፳፮፥፫፤ ፳፰፥፲፫፤ ፴፭፥፲፪)

የአብርሃም ዘር የከነዓንን ምድር ከመውረሱ በፊት ግን በግብፅ ለ፬፻፴

www.ethiopianorthodox.org

ዓመታት በባርነት እንደሚሰቃዩና እግዚአብሔርም በታላቅ ተአምር በብዙ ሀብት እንደሚያወጣቸው ተገልጿል። (ዘፍ.፲፭፥፲፫–፲፮፤ ዘጸአ. ፲፪፥፵፤ ሐዋ.፯፥፮) በዚህ መሠረት በረሃብ ምክንያት በያዕቆብ ዘመን ወደ ግብፅ ተሰደው በባርነት ሲሰቃዩ ከ፬፻፴ ዘመን በኋላ በሙሴ መሪነት ከግብፅ ሲያወጣቸው በኢያሱ መሪነት ደግሞ ወተትና ማር የምታፈሰውን ከነዓንን አውርሶአቸዋል። (ዘጸ.፫፥፯–፱፤ ኢያ.፩፥፩–፱) እግዚአብሔር ለጊዜው እንደተስፋ ቃሉ አሕዛብን አባርሮ ለእሥራኤላውያን ከነዓንን ቢያወርሳቸውም ይህ የተስፋው ፍፃሜ ነበር ማለት አይደለም። የበለጠውን ሰማያዊ ሀገር ስላዘጋጀላቸው እርሷን ይናፍቁ ነበር። እውነተኛዋ የተስፋ ሀገር የሰው ዘር ሁሉ ሊናፍቃትና ተስፋ ሊያደርጋት የሚገባ መንግሥተ ሰማያት (ሰማያዊት ኢየሩሳሌም) ናት። አብርሃምም በምድራዊቷ የተስፋይቱ ምድር አንፃር ሰማያዊቷን የተስፋ ሀገር ለመውረስ ተስፋ ያደርግ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንኑ ሲገልጽ «አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ሥፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ። ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ ለእንግዶች እንደሚሆን በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ ያን የተስፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር እንደመጻተኛ ተቀመጠ። መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና» (ዕብ.፲፩፥፲) «ያን የወጡበትን አገር አስበው በሆኑ ሊመለሱ ጊዜ በሆነላቸው ነበር። አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ» ብሎአል። (ዕብ.፲፩፥፲፭–፲፮)

እግዚአብሔር እሥራኤል ዘሥጋን ከግብፅ ባርነት በሙሴ መሪነት አውጥቶ በኢያሱ መሪነት ምድራዊት ኢየሩሳሌምን እንዳወረሳቸው እንዲሁም በአዲስ ኪዳንም ከቤተ አብርሃም ከተወለደችው ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ እሥራኤል ዘነፍስን ከሲኦል በደሙ ነፃ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደገነት (መንግሥተ ሰማያት) አግብቶአቸዋል። በዚሁ ጊዜ አብርሃም ይናፈቃት የነበረችይቱን ገነትን አግኝቶአታል። እኛም ምድራዊ ርስት የምንናፍቅ ሳይሆን ከዚህ ዓለም ባሻገር ያለችውን በእምነት ያየናትን ሀገር እንናፍቃለን። «ድንኳን የሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለን እናውቃለን።» (፪ቆሮ.፭፥፩) «እኛ ሀገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም የሚመጣ መድኃኒትን እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን» (ፊልጵ.፫፥፳) «በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን።» (ዕብ.፲፫፥፲፬) በማለት ቅዱስ ጳውሎስ በሚገባ ገልጿታል።

እንግዲህ በክርስቶስ አምነው ትእዛዙን ጠብቀው በሃይማኖት የአብርሃም ልጆች የሆኑ ሁሉ የአብርሃም የተስፋው ወራሾች ናቸውና እርሱ ከገባበት ሰማያዊት ሀገር ይገባሉ። ይህንንም በሉቃ.፲፮፥፳፪–፳፫ በተጠቀሰው ታሪክ አልአዛር ከሞተ በኋላ መላዕክት ነፍሱን ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት በማለት ይገልፃል። በተጨማሪም በማቴ.፰፥፲–፲፩ ላይ መድኃኒታችን ሲናገር «እውነት እውነት እላችኋለሁ...ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ» በማለት አረጋግጧል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ዘሥጋ ምድራዊት ኢየሩሳሌምን [illegible] ራኤል ዘነፍስ ደግሞ ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ያወርሳቸዋል። ይህ ጸጋ የተገኘው ከድንግል ማርያም ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ (ቤዛነት) ነው። (ዕብ.፲፪፥፳፪)

ሐ. «ለአንተና ለዘርህ አምላክ እሆናለሁ» ክቡር ዳዊት በመዝሙር «እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ፤ እርሱ ለርስቱ የመረጠው ሕዝብ ምስጉን ነው።» ብሏል (መዝ.፴፪፥፲፪) አብርሃም ከወገኖቹ ተለይቶ ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር በመመለሱ፤ ፈጣሪውን በማወቁና በማመኑ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ አምላክ እንደሚሆን ቃል ገባለት። እግዚአብሔር የሁሉም ፈጣሪ ቢሆንም በተለይ የቅዱሳን መላእክት፣ የጻድቃን፣ የነቢያት፣ የሐዋርያት...አምላክ ተብሎ ቢጠራ ይወዳል። ስለዚህ አምላከ ሚካኤል ወገብርኤል፤ አምላከ ሱራፌል ወኪሩቤል አምላከ ነቢያት ወሐዋርያት፤ አምላከ ጻድቃን ወሰማዕታት...ተብሎ ይጠራል። ይሁንንም ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሲጠራ አያፍርም። ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና።» በማለት ገልጾታል። (ዕብ.፲፩፥፲፮) ስለዚህ ባለቤቱ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና በተገለጸለት ጊዜ «እኔ የአባቶችህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ» በማለት ራሱን ገልጾለታል፤ (ዘጸ.፫፥፮፤ ማቴ.፳፪፥፴፪) በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለልጆቹ አምላክ በመሆኑ እስራኤላውያንን ሕዝቤ ይላቸው ነበር። ጠላቶቻቸውን እያጠፋ ከተማረኩበት ነጻ ያወጣቸው ነበር። በመሆኑም ከ፬፻፴ ዓመታት ባርነት በኋላ ከግብፅ አውጥቶ ወተትና ማር የምታፈሰውን ምድረ ርስት አውርሶአቸዋል። እግዚአብሔር አምላኩ

www.ethiopianorthodox.org

የሚሆንለት ሕዝብ የሚያጣው፣ የሚፈራውና የሚቸግርው ነገር የለም። በሃይማኖት የአብርሃም ልጆች የሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ አምላካቸው እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ከግብርናተ ዲያቢሎስ በተቀደሰ ደሙ ነፃ አውጥቶአቸዋል። የተስፋይቱን ሀገር ገነት (መንግሥተ ሰማያትን) አውርሶአቸዋል ያወርሳቸዋልም።

እግዚአብሔር ለተገረዙት ለአብርሃም ልጆች (ለእሥራኤል ዘሥጋ) ብቻ ሳይሆን ላልተገረዙት ለአሕዛብም በስሙ አምነው ተጠምቀው በሃይማኖት የአብርሃም ልጆች ለሆኑት ሁሉ አምላክ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ «እምነቱ ለአብርሃም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት እንላለንና። እንዴት ተቆጠረለት? ተገርዞ ሳለ ነውን ወይስ ሳይገረዝ? ተገርዞስ አይደለም ሳይገረዝ ነበር እንጂ። ሳይገረዝ በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ። ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው። ይኸውም ለተገረዙት ብቻ አይደለም ነገር ግን አባታችን አብርሃም ሳይገረዝ የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው» በማለት ዘርዝሮ አስረድቷል። (ሮሜ.፬፥፱–፲፪፤ ፲፭፥፯–፲፫) የአብርሃም ተስፋና በረከት ለአሕዛብ እንደተረፈ በዚህ ሁሉ እንርዳለን። የአብርሃም በረከት ለአሕዛብ የተረፈው ከአብርሃም ዘር ከተወለደችው ከድንግል ማርያም በተወለደው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ድንግል ማርያም የአብርሃም ተስፋ መፈጸሚያና የአሕዛብ በረከት ማግኛ ምክንያት መሆኗን እንርዳለን።

መ. «በአንተና በዘርህ የምድር አሕዛብ ይባረካሉ።» እግዚአብሔር ለአብርሃም ይህንን ቃል ኪዳን ሲገባለት አብርሃምን የበረከት ምክንያት እንዳደረገው እንረዳለን። የምድርን አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔር በአብርሃምና በዘሩ በኩል እንደሚባርክ ማቀዱ የአብርሃምን ታላቅነት ይመሰክራል። አብርሃምን የበረከት ምክንያት ሲያደርገው «ታላቅ ሕዝብም አደርግሀለሁ እባርክሀለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» ብሎታል። (ዘፍ.፲፪፥፪–፫) ይህንኑ ቃል ኪዳን ለይስሐቅና ለያዕቆብም አጽንቶላቸዋል። (ዘፍ.፳፪፥፲፰፤ ፳፮፥፬፤ ፳፰፥፬) ለአብርሃም ይህን ያህል ክብር የተሰጠው እመቤታችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወገቡ ስላሉ ነው። እግዚአብሔር ከአብርሃም ባሕርይ ዓለምን ከመርገም የሚያድንበትና ለዓለም በረከት የሚያድልበት ዘር ማዘጋጀቱን በልዩ ልዩ ቦታ ገልጿል። «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደሰዶም በሆንን እንደገሞራም በመሰልን ነበር።» በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ ተናግሯል። (ኢሳ.፩፥፱) የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ዓለምን ለማዳን በወደደ ጊዜ የአብርሃም ዘር ከሆነችው ለእናትነት ካዘጋጀት ከሴቶች ሁሉ ከመረጣትና ካከበራት ከድንግል ማርያም ሰው ሆኖ በሥጋ የአብርሃም ዘር ተብሎ በሞቱ ዓለምን ሁሉ አድኖአል። የእግዚአብሔር ልጅ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ተዋሕዶ ባያድነን ኖሮ፤ እመቤታችንን ለዚህ ተዋሕዶ ከአብርሃም ዘር መርጦ፣ አክብሮ ባያዘጋጃት ኖሮ በነፍስም በሥጋም በጠፋን ነበር። ቅዱስ ጳውሎስም የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው መሆን ሲገልጽ «የነጣውን ከመላእክት የነሣው አይደለምና ከአብርናም ዘር እንጅ» ብሏል። (ዕብ.፪፥፲፮፤ ፩፥፩–፫) ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት በጻፈበት አንቀጽ «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ » ብሎ ከአብርሃም እስከ ዮሴፍ ያለውን የትውልድ ሐረግ ቆጥሮ ክርስቶስ ያለወንድ ዘር ከድንግል ማርያም መወለዱን አስረድቷል። (ማቴ.፩፥፩–፳፭) ለሕዝብና ለአሕዛብ መድኃኒተ ሥጋ መድኃኒተ ነፍስ የሆነውና በተስፋ ሲጠበቅ የነበረው «መሲህ» ጊዜው ሲደርስ ከድንግል ተወለደ። በዚህም የአብርሃም ተስፋ በድንግል ማርያም ተፈፀመ። ድንግል ማርያም ነቢያት ትንቢት የተናገሩለትን፤ ሱባዔ የቆጠሩለትን፤ ምሳሌ የመሰሉለትን አምላክ በመውለዷ የነቢያት የትንቢታቸው መፈጸሚያ ሆናለች። ስለዚህ ድንግል ማርያም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ላገኘነው ጸጋና በረከት ሁሉ ምክንያት እሷ ናትና የተሰጣት ክብር እጅግ ታላቅ ነው። የሚባርኳት ይባረካሉ የሚረግሟት ይረገማሉ።

ለሰው ልጅ ሁሉ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያድለው የአብርሃም ዘር የተባለው የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ ክታቡ ውስጥ «መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም ሰበከ... ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ ስለብዙዎች እንደሚነገር ለዘሮቹም አይልም ለአንድ እንደሚነገር ለዘርህም ይላል። እርሱም ክርስቶስ» ብሏል። (ገላ.፫፥፰ እና ፲፮) ስለዚህ ከአብርሃም ዘር ተገኝታ የአብርሃምን ዘር ኢየሱስ ክርስቶስን ወልዳ ስላስገኘች የአብርሃም ተስፋ ሙሉ በሙሉ የተፈጸመባት የቃል ኪዳን ፍፃሜ ናት። ✣

ተከታይ የሌለው የአብ ባሕርይ ልጁ ነው። ሰው የሆነው አምላክ (ሥጋው ቃል) ሰማይና ምድር የማይችሉት ሲሆን በለበሰው ሥጋ በድንግል ጀርባ ታዝሎ ወደ ግብፅ ተሰደደ። እመቤታችን ፈጣን ደመና (ደመና መፍጢንት) መባሏ ሰውን ለማግለድ፤ ለመርዳት ፈጣን ስለሆነች ነው። «አፍጣኒተ ርድኤት ማርያም በጊዜ ምንዳቤ ወአጸባ ለዓይን እምቀራንባ...» እንዳለ ደራሲ። ትርጉም በችግር በመከራ ጊዜ እንደዓይን ጥቅሻ ፈጥና ረድኤትን የምታመጣ ማርያም ማለት ነው። ጌታችን በሕፃንነቱ ወደ ግብጽ በተሰደደ ጊዜ የግብጽ ጣኦታት ወድቀዋል ፈርሰዋል ደቀዋል።

አንድም ደመና ኖኅ አንቺ ነሽ ቅዱስ ኤፍሬም አያይዞ «ትእምርተ ዋሕዱ ረሰየኪ አብ» ትርጉሙ «አብ የልጁ ምልክት አደረገሽ ማለት ነው።» ይህን ሲተረጉሙት በቀስትነት ሳለሽ አብ የዕርቅ ምልክት አደረገሽ ማለት ነው። ለኖኅ የተሰጠችው ቀስተ ደመና የዕርቅ፤ የሰላም ምልክትና ማኀተም ናት። ያች ደመና ቀስት የተባለችው እንደደጋን ያለ ቅርጽ ስላላት ነው። የዕርቅ ምልክት የሆነችውም እንደሚከተለው ነው። አንድ ቀስት የያዘ ሰው ጠላቱን አይቶ ለመውጋት የፈለገ እንደሆነ ደጋኑን ወደጠላቱ አድርጐ ቀስቱን ከመወጠሪያው (ከአውታሩ) ላይ ሰክቶ አነጣጥሮ ይለጥጠዋል። የሚወደውን ሰው ካየ ደጋኑን ወደራሱ አውታሩን ወደወዳጁ ያዞራል። ልብ ብለን ብንመለከት የኖኅ ቀስተ ደመና የዕርቅና የሰላም ምልክትነቱ የተሟላ ነው። የቀስተ ደመናውን ደጋን ወደ ሰማይ ወደራሱ ወደ እግዚአብሔር አዙሮ አውታሩን ወደእኛ ወደመሬት አድርጐ ይታያል። ይህች በተለያዩ ሕብረ ቀለማት ያሸበረቀች ቀስተ ደመና የእመቤታችን ምሳሌ ናት። እመቤታችን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለች የዕርቅ የሰላም ምልክት ናት። እግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ከድንግል ማርያም የነሳውን (የተዋሐደውን) ትስብእት በዕሪናው አኑር ከእንግዲህ የልጄን ዘመዶች በውሃ አላጠፋም ሲል የቀስተ ደመናውን ደጋን ወደ ላይ አድረጐ ታይቶልናል። ከዚህች ቀስተ ደመና አራቱ ሕብረ ቀለም ጐልቶ መታየቱ ጌታችን አራቱን ባሕርያተ ሥጋ ከእመቤታችን ለመንሣቱ ሕብሩ ሰባት ነው ቢሉ ጌታችን ሰባቱን ባሕርያት (አራቱን ባሕርያተ ሥጋና ሦስቱን ባሕርያተ ነፍስ) ከእመቤታችን ለመንሳቱ ምሳሌ ነው። ቀስተ ደመና በምድር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የክብር ዙፋንም እንደማይለይ ነቢዩ ሕዝቅኤል ገልጾልናል። «በራሳቸውም በላይ ካለው ጠፈር በላይ የሰንፔር ድንጋይ የሚመስል የዙፋን አምሳያ ነበር በዙፋኑም አምሳያ ላይ እንደሰው መልክ አምሳያ ነበር... በዙሪያውም ፀዳል ነበር። በዝናብ ቀን በደመና ውስጥ እንደቀስተ ደመና አምሳያ እንዲሁ በዙሪያው ያለ ፀዳል አምሳያ ነበር። የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ ይህ ነበር።» (ሕዝ.፩፥፳፮–፳፰) ይላል። ይህ የሕዝቅኤል ራዕይ የዳዊትን ትንቢት ያስታውሰናል። ይኸውም በመዝ.፵፬፥፱ ላይ «በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፍና ንግስቲቱ በቀኝህ ትቆማለች» ይላል። ይህም ሲተረጐም ንግሥተ ሰማይ ወምድር እመቤታችን በሰጠሃት ክብር ጸንታ ትኖራለች በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋ ማለት በንጽሐ ሥጋ በንጽሐ ነፍስ በንጽሐ ልቦና ተሸልማ ተሸላልማ በልጇ አጠገብ በክብር መገኘቷን መናገር ነው። ሕዝቅኤል ቀስተ ደመና በእግዚአብሔር ዙፋን ዘንድ እንዳየ እመቤታችንም እንደ ዳዊት ቃል ከልጇ ዙፋን አትለይም።

እንግዲህ በሕይወታችን ውስጥ እመቤታችንን ከልብ ከወደድን፣ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ስለ ድንግል ማርያም የምታምነውንና የምታስተምረውን ሳንጠራጠር በፍጹም ልባችን ካመንን ቀስተ መሃላሁ ለኖኅ የተባለች ድንግል ማርያም የምሕረት የሰላም ቃል ኪዳን ይዛ ትመጣልናለች። ደመና ኤልያስ የተባለች ድንግል ማርያም የሕይወት ዝናምን (በረከተ እግዚአብሔርን) ታዝንምልናለች። ደመና መፍጠኒት የተባለች ድንግል ማርያም ረድኤተ እግዚአብሔርን ወደኛ በፍጥነት ታስተላልፍልናለች። ከእመቤታችን ረድኤትና በረከት ጣዕምና ፍቅር የተለዩትን ሰዎች ቅዱስ ጴጥሮስ «ደፋሮችና ኩሩዎች ሆነው ሥልጣን ያላቸውን ሲሳደቡ አይንቀጠቀጡም...አእምሮ እንደሌላቸው እንስሶች ሆነው በማያውቁት ነገር እየተሳደቡ በጥፋታቸው ይጠፋሉ።» ብሏቸዋል። ቅዱስ ይሁዳም «እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ።...እነዚህ በነፋስ የተወሰዱ ውሃ የሌለባቸው ደመናዎች፤ ፍሬ የማያፈሩ፤ ሁለት ጊዜ የሞቱ፤ ከነሥራቸው የተነቀሉ፤ በበጋ የደረቁ ዛፎች፤ የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር ማዕበል ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው።» ብሎአቸዋል። (፪ጴጥ.፪፥፲፩–፲፪፤ ይሁዳ.፲፥፲፫)

ኪዳን ኖኅ ፍጹም ትርጉም ያገኘውና ሙሉ የሆነው በኪዳን ምሕረት መሆኑንና የኖኅ ታሪክ እግዚአብሔር በድንግል እናቱ አማካኝነት ለፈጸመው ዓለምን የማዳን ሥራ ምሳሌ እንደነበር አይተናል። ልዑል እግዚአብሔር በእመቤታችን አማላጅነት በቸርነቱ ከጠላታችን ከዲያቢሎስ ተንኮል ይሰውረን። አሜን። ✣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ይቀጥላል

www.ethiopianorthodox.org